# የኮንትራት ወይም የጊዚያዊ ሠራተኛ ነዎት?



በ ☎ 131202 የርስዎን ቋንቋ እንናገራለን

*Are you a contract or casual worker?* – **Amharic**

ከዚህ በታች ባሉት የገቢ መደጎሚያ ለማግኘት ካመለከቱ ክፍያውን ከማግኘትዎ በፊት ጊዜ ሊያስጠብቅዎት ይችላል:

- Newstart Allowance /ለሥራ መፈለጊያ አበል
- Youth Allowance /ለወጣት አበል
- Austudy /ለተማሪ አበል
- Sickness Allowance /ለሕመምተኛ አበል
- Carer Payment /ለተንከባካቢ አበል
- Special Benefit /የልዩ ክፍያ (በእጩነት የቀረበ ቪዛ ላላቸው ብቻ)
- Disability Support Pension /ለአካለጎደሎ የድጋፍ ጡሮታ (ከዓይነ ስውር ደንበኞች ባሻገር)
- Parenting Payment /ለአሳዳጊ ክፍያ፣ ወይም
- Widow Allowance /ባሏ ለሞተባት አበል ይሆናል።

ባለቤትዎ ወይም እርስዎ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ የሆነ ኮንትራት ወይም የጊያዊ ሥራ ከሠሩ ታዲያ የሚቀጥለውን ክፍያ ከማግኘትዎ በፊት የተወሰነ ጊዜ ያስጠብቅዎታል። ይህ የጊዜ ጥበቃ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በወቅታዊ ሠራተኞች ላይ ሲተገበር፣ እንዲሁም ከመስከረም/ September 20 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ለኮንትራትና በጊዚያዊ ሠራተኞች ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

## የኮንትራት ወይም የጊዚያዊ ሠራተኛ ምን'ድ ነው?

**የኮንትራት ሠራተኛ፤** ለተወሰነ ጊዜና ተግባር የሚካሄድ ማንኛውም የኮንትራት ሥራ ሲሆን ሥራውን ለሌላ ማኮናተርንም ያካትታል።

**የጊዚያዊ ሥራ** (ወይም የሚቆራረጥ ሥራ) ይህ አልፎ አልፎ የሚገኝ ሥራ ሲሆን መቸ እንደሚያልቅ ለመገመት የሚያስቸግር አስቸጋሪና ከአንድ ዓመት በታችና የእረፍት ጊዜ ለማግኘት የማይቻልበት ሥራ ይሆናል።

**በኮንትራትና በጊዚያዊ ሥራ ላይ ሊካተት የሚችል:**

- በየጊዜው የመዘጋት ችግር ያለበት ሥራ - እንደ በፋብሪካ ውስጥ ሥራ በገና በዓልና ለጥገና በየጊዜው በሚዘጋ
- በየጊዜው የሚቆምና የሚጀምር ማንኛውም ሥራ- እንደ የማእድን ሥራና የዘይት ኢንዱስትሪዎች
- የማያቋርጥ ሥራ ወይም ሥራ የሌለበት ጊዜ ሲገመት
- በችግር የሚተካ ሥራ – እንደ ለማስተማር ወይም ለጤና ጥበቃ ሥራ ተክቶ መሥራት
- የመማክርት ሥራ
- መልሶ ማኮናተርን ያካተተ የኮንትራት ሥራ
- የጤናና ሕክምና ሠራተኞች፣ እና
- በስነ-ጥበብና በማዝናኛ መስክ የኮንትራት ሥራ ይሆናል።

## የጊዜ ማስጠበቁ በርስዎ ላይ ይጠየቃልን?

የሚከተሉትን ካሟሉ የጊዜ ማስጠበቁ በርስዎ ላይ ተግባራዎ አይሆንም:

- በሥራው ላይ ከአንድ ዓመት በላይ ከቆዩ፣ ወይም
- በኮንትራት ወይም በጊዚያዊ ሠራተኛነት የተከማቸ የእረፍት ጊዜ ማግኘት ከቻሉ።

የጊዜ ማስጠበቁ ተግባራዊ የሚሆነው:

- የሚሠሩት ተግባር ከኮንትራት ወይም የጊዚያዊ ሥራ ጋር የሚስማማ ከሆነ እና
- በዚህ ሥራ ያገኙት የነበረው ክፍያ ከሳምንታዊ የመደበኛ ጊዜ አማካኝ ገቢዎች (AWOTE)* በላይ ከሆነ ይሆናል።

ጊዜ መጠበቁ በርስዎ ላይ ተግባራዊ ከሆነ ታዲያ ክፍያ ከማግኘትዎ በፊት ምን ያህል ጊዜ እንደሚጠብቁ በCentrelink/ ሴንተርሊንክ በኩል ስሌት ይደረጋል።

**በጊዜ መጠበቁ ላይ አንዳንድ የተለየ ሁኔታ ሲኖር እነዚህም በቃለመጠይቁ ላይ ገለጻ ይደረጋል።**

* ሳምንታዊ የመደበኛ ጊዜ አማካኝ ገቢዎች (AWOTE) አውስትራሊያኖች በሳምንንቱ መደበኛ አማካኝ ገቢዎች በተመለከተ የአውስትራሊያ ስታቲስቲክስ እርምጃ ቢሮ ነው። በ2006 ዓ.ም የአበል ክፍያን ለማመልከት የAWOTE ጠቃሚ የገንዘብ ገቢ መጠን በሳምንት $1022.60 ዶላር ትዳር ለሌልው እና ለባለ ትዳር በሳምንት $2045.20 ዶላር ይሆናል። ይህ የአሃዝ መጠን በየዓመቱ ይስተካከላል። የጥበቃው ጊዜ እንዴት እንደሚሰላ በሚከተለው ምሳሌ ይታያል።

# የጊዜ ጥበቃው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

ይህ ከሥራ ባገኙት የገቢ መጠን እና ለምን ያህል ጊዜ ይሠሩ እንደነበር ታይቶ ይወሰናል።

በሥራ ላይ ያገኙት የገቢ መጠን ከ AWOTE በላይ ከሆነ የአበል ክፍያ ከማግኘትዎ በፊት ትንሽ ጊዜ ሊያስጠብቅዎት ይችላል።

የጊዜ ጥበቃው እንዴት እንደሚሰላ በሚከተለው ምሳሌ ላይ ይታያል።

## ምሳሌ 1

ራቸል/Rachel የምትባል በሆቴል ውስጥ ለስምንት ሳምንታት ሠራች። ከዚያ ሥራ ስለሌላት Newstart Allowance/የሥራ መፈለጊያ አበል ጠየቀች። በምትሠራበት ጊዜ ያገኘችው ጠቅላላ ገቢ $12 288 ዶላር ነው።

ለራቸል የሚያስጠብቃት ጊዜ እንደሚከተለው ታስቦ ይወሰናል:

ደረጃ 1: ከሥራ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ በ AWOTE ($1022.60) ይካፈላል፣ ይህም $12 288 ÷ $1022.60 = 12.01 ሳምንታት
(ይህ ማለት ራቸል ለ12.01 ሳምንታት ያገኘችው ገቢ ከAWOTE ጋር ተመሳሳይ ይሆናል)

ደረጃ 2: 12.0ሳምንታት — ራቸል ለስምንት ሳምንታት የሠራችው = 4.01 ሳምንታት ይሆናል

ይህ መጠን ወደ ሙሉ ቁጥር ሲጠጋጋ ወደ አራት ሳምንታት ሲሆን ለራቸል የተሻለ ጥቅም አለው።

ራቸል Newstart Allowance/የሥራ መፈለጊያ አበል ክፍያ ከማግኘቷ በፊት ሥራዋን ካቆመችበት ቀን ጀምሮ ለአራት ሳምንታት መቆየት ያስፈልጋል።

## ምሳሌ 2

ዳረን/Darren ያገባና በህንጻ ሥራ ላይ ለ16 ሳምንታት ይሠራል። ሌላ ሥራ ስለሌለው ለ Newstart Allowance/ ለሥራ መፈለጊያ አበል ያመለክታል። በዚህን ጊዜ ጠቅላላ ገቢው $34 234 ዶላር ነው። የዳረን ሚስት፣ ጁሊ/ Julie ደግሞ የጊዚያዊ ሂሳብ ሥራ በጥቂቱ ትሠራለች። በ16 ሳምንታት ዳረን በህንጻ ሥራው ላይ እያለ ያገኘችው የገቢ መጠን $9376 ዶላር ይሆናል። የዳረን ሥራ በሚያልቅበት ጊዜ ሁለቱም ባለትዳሮች ለ Newstart Allowance/ለሥራ መፈለጊያ አበል ያመለክታሉ።

የሚያስጠብቃቸው ጊዜ እንደሚከተለው ታስቦ ይወ

ሰናል:

ደረጃ 1: የዳረንን እና የጁሊን ጠቅላላ ገቢ መደመር፣ $34 234 + $9376 = $43 610 ዶላር

ደረጃ 2: ሁለቱም ያገኙትን ገቢ በ AWOTE ($2045.20) ይካፈላል፣ ይህም ለባለትዳር $2045.20
$43 610 ÷ $2045.20 = 21.32 ሳምንታት

ደረጃ 3: 21.32 ሳምንታት — ለ16 ሳምንታት ዳረን የሠራው = 5.32 ሳምንታት ይሆናል።

ይህ መጠን ወደ ሙሉ ቁጥር ወደ አምስት ሳምንታት የተጠጋጋ ነው።

ዳረንና ጂሊ Newstart Allowance/የሥራ መፈለጊያ አበል ክፍያ ከማግኘቷ በፊት ዳረን ሥራውን ካቆመበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ሳምንታት መቆየት ያስፈልጋቸዋል።

## ምሳሌ 3

ብሪያን/ Brian ያላገባና በተተኪ የነርስ ሥራ ላይ ለ26 ሳምንታት ይሠራል። ሥራራውን ከስድስት ሳምንት በፊት ሲጨርስ፣ ሌላ ሥራ ከመፈለጉ በፊት እረፍት ለመውሰድ ስለወሰነ በአሁን ጊዜ Newstart Allowance/የሥራ መፈለጊያ አበል እንዲሰጠው ማመልከት ብቻ ይሆናል። በዚህን ጊዜ ጠቅላላ ገቢው $30 585 ዶላር ነበር።

የሚያስጠቀው ጊዜ እንደሚከተለው ታስቦ ይወሰናል:

ደረጃ 1: ከሥራ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ በ AWOTE ($1022.60 ዶላር) ማካፈል፣ ይህም $30 585 ÷ $1022.60 = 29.90 ሳምንታት

ደረጃ 2: 29.90 ሳምንታት — ለ26 ሳምንታት ብሪያን የሠራው= 3.90 ሳምንታት ይሆናል።

ይህ መጠን ወደ ሙሉ ቁጥር ሲጠጋጋ ወደ ሶስት ሳምንታት ይሆናል።

ይህ ሶስት ሳምንት ብሪያን ሥራ ካቆመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል። ታዲያ ብሪያን Newstart Allowance/የሥራ መፈለጊያ አበል ክፍያ ከማግኘቱ በፊት መቆየት አይኖርበትም፣ ምክንያቱም ሥራ ካቆመበት ቀን ጀምሮ ስድስት ሳምንታት ስላለፈ ይሆናል።

## ለ Centrelink/ሴንተርሊን ማቅረብ ያለብዎት ምን'ድ ነው?

ባለቤትዎ ወይም እርስዎ የኮንትራት ወይም የጊዚያዊ ሥራን ሲጨርሱ በስድስት ወር ውስጥ ባለው ጊዜ አበል እንዲሰጥዎ ከጠየቁ፣ ከዚህ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃ የሚጠይቅ ቅጽ ሞልተው ለ Centrelink/ሴንተርሊንክ ማቅረብ አለብዎ:

- ምን አይነት ሥራ (እርስዎና ወይም ባለቤትዎ) እና ለማን እንደሠሩ
- ሥራውን መቸ ጀምረው እንደጨረሱ
- በወቅቱ ከግብር በፊት ጠቅላላ ገቢዎን እና
- ማንኛውም የተቆረጠ ገንዘብና እንዲመለስልዎ ለመጠየቅ የሚቻል (በአውስትራሊያ የግብር ጽ/ቤት እንደሚፈቅደው)።

በተጨማሪም ለሰጡት መረጃ የሚገልጽ ማቅረብ ማለት የተከፈለበት ወረቀት (payslips)፣ የዋጋ መጠየቂያ ደረሰኝ፣ የዓመት ገቢ ምስክር ወረቀት (group certificates)፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ጽሁፍ፣ የደመወዝ መመዝገቢያ፣ የባንክ መግለጫ ጽሁፍ፣ የሰዓት መመዝገቢያ ወረቀት ወይም ከቀጣሪዎ ደብዳቤ ማቅረብ ይሆናል።

በነዚህ ለውጦች ሳቢያ ሚቸገሩ ከሆነና ካልተረዳዎ በበለጠ መረጃ ለማግኘት Centrelink/ሴንተርሊንክን ያነጋግሩ። የጊዜ ገደቡ እስኪደርስ ሲጠብቁ የገንዘብ ችግር ካጋጠምዎት ወይም በባጀት አጠቃቀም ላይ እርዳታ ካስፈለገ Centrelink/ሴንተርሊንክን ማነጋገር ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ ችግር ያለባቸው ሠራተኞች ቀጣሪ ከሆኑ ስለ ሥራቸው በተመለከተ ማስረጃ ለ Centrelink/ሴንተርሊንክ እንዲሰጡ ይጠየቁ ይሆናል። የሆነ ጥያቄ ካለዎት እባክዎ በCentrelink/ ሴንተርሊንክ ሥራ ሆት መስመር 13 1158 ደውሎ ማነጋገር።

## የክህደት ቃል/ Disclaimer

በዚህ የሕትመት ጽሁፍ ያለው መረጃ ስለሚቀርበው ክፍያ እንደ መመሪያ እንዲያገለግል ስለተፈለገ ብቻ ነው።

የርስዎ ኃላፊነቶች ምን'ድ ናቸው?

- በተለይ እርስዎ ያሉበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የክፍያ ማመልከቻ ማስገባት ከፈለጉ ለመወሰን የርስዎ ኃላፊነት ይሆናል።
- መረጃው ከመስከረም/ September 2006 ዓ.ም ጀምሮ ትክክለኛ ቢሆንም በርግጥ ለውጥ ሊኖር ይችላል።

**አበል የሚከፈለው ከየትኛው ቀን ጀምሮ ነው?**

አብዛኛው የመንግሥት ክፍያ የሚሰጠው ማመልከቻው ከገባበት ወይም ከዚያ በኃላ ይሆናል። ስለዚህ ቀድመው ማመልከቻውን ካስገቡ በተሎ ሊከፈልዎት ይችላል።

**በሶስተኛ አካል ጉዳዩን የሚያካሂዱ ከሆነ ሁኔታው ምን ይመስላል?**

የ Centrelink/ሴንተርሊንክ ሠራተኛ ባልሆነ ሶስተኛ አካል ጉዳዩን ማካሄድ ይቻል ይሆናል። ይህን ካደረጉ፣ እባክዎ ያስተውሉ፤ ስለ ክፍያዎ መረጃ ወይም ምክር በማንኛውም ሶስተኛ አካል በኩል እንዲቀርብልዎት Centrelink/ ሴንተርሊንክ አይፈቅድም።

Centrelink/ሴንተሊንክን ከእንግሊዝኛ ባሻገር በሌላ ቋንቋዎች ለማነጋገር በቁጥር 13 1202* መደወል። እንዲሁም በራስዎ ቋንቋ መረጃ በዌብሳይት www.centrelink.gov.au ላይ ይገኛል።

* በአውስትራሊያ ማንኛውም ቦታ ሆኖና በመደበኛ ስልክ መገልገያ ሆነው በቁጥር "13" ሲደውሉ ከአካባቢ ስልክ ጥሪ ዋጋ በላይ አይሆንም (የስልክ ጥሪው ዋጋ እንደ የስልክ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ይለያያል)። በቁጥር "1800" ሲደውሉ አያስከፍልም። በህዝብ የስልክ መገልገያ ወይም በሞባይል ሲደውሉ ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላል።